ኅብር ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ[ኅብር ኢትዮጵያ]
HIBIR ETHIOPIA DEMOCRATIC PARTY [HIBIR ETHIOPIA]

http://www.hibirethiopia.com hibirethiopia2@gmail.com

## መንግሥት የህግ የበላይነት የማስከበር ኃላፊነቱን ለመወጣት አልቻለም፤ የብሄራዊ መግባባትና ዕርቀ ሠላም መድረክ በአስቸኳይ

ፓርቲያችን ኅብር ኢትዮጵያ በአገራችን የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ እውን በማድረግ በህዝብ መፈቃቀድ፣ መከባበርና እኩልነት ላይ የተመሰረተች የህግ የበላይነት የተከበረባት ለሁሉም ዜጎች የምትመች በአገራዊ እሴቶች ላይ የቆመች ፌዴራላዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት ግብ አድርጎ በ 5 ፓርቲዎች ውህደት የተመሰረተ አገራዊ ፓርቲ ነው፡፡

ፓርቲያችን ኅብር ኢትዮጵያ ከምስረታው ዕለት ጀምሮ የለውጡ ኃይል ሊከተል የሚገባውን ሃቀኛ ዴሞክራሲያዊ የለውጥ አቅጣጫና ሂደት ምን ሊሆን እንደሚገባ ሲጠቁም፣ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ መግባባትና ዕርቅ መሰረት ያደረገ ተቋማዊ ለውጥ እንዲሆን ሲያመላክት፣ ከጅምሩ ለተለያዩ የመንግስት ከፍተኛ አመራሮች በአካልና በደብዳቤ እንዲሁም የአገራችን ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታ በመገምገም ባወጣናቸው መግለጫዎች መንግስት ዲሞክራሲን፣ የህግ የበላይነትን ለድርድር እንዳያቀርብና ሊያስከትል የሚችለውን አገራዊ አደጋ ሲያመላክትና ጅምሩን ለውጥ ለማገዝ አገራዊ አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል፡፡

በመግለጫዎቻችን «…አገራችን በሪፎርም ውስጥ መሆኗን፣ይህ ሪፎርም መቀጠል ያለበት መሆኑን፣ ማስቀጠሉ የሁሉም ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ እንደሚጠይቅ፣ ነገር ግን በሪፎርሙ ሂደት የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ መዘፈቃችን፣ ለከፍተኛ ማኅበራዊ ቀውስና ኢኮኖሚያዊ ውድመት ከመዳረግ, በተጨማሪ የአገራችን ህልውና አደጋ ላይ መውደቁን…» በመግለጽ አገራችን ከዚህ የህልውና አደጋ ለመታደግና አንድነቷን ለመጠበቅ ገዢው ፓርቲ በተናጠል የሚቻለው ባለመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከዚህ አረንቋ ለመውጣት በጋራ እንድንረባረብ» ጥሪ አድርገናል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥሪ በተለይ በመንግሥት ባለመደመጡ ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን ከድጡ ወደ ማጡ እየገባ፣ ዛሬ አገሪቱ በሁለት መንግስት የምትተዳደር ከሚመስል ደረጃ ደርሰናል፤በአንድ ማኅበራዊ ሚዲያ የተላለፈ መልዕክት፤ በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ለብዙ አስርታት ዜጎች እልቂትና- ለመቶዎች አካል ጉዳትና መፈናቀል፣ እንዲሁም በቢሊዮኖች ብር ለሚገመት ሃብት ውድመት ስንዳረግ፣ በኃይማኖት ተኮር ግጭቶች ምዕመናን ተገድለው፣ ቤተ እምነቶች ላይ ጥቃት ሲፈጸም በተጨባጭ ተመልክተናል፡፡

የዚህ ዋነኛ መነሻ ከጅምሩ በጠቅላይ ሚ/ር ዐቢይ የሚመራው የለውጥ ኃይል በአገር ቤት በግንባር ዋጋ ከከፈሉት ሠላማዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይልቅ በውጪ ሆነው ይታገሉ ለነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይም በትጥቅ ትግል ተሰማርተናል ላሉት እንዲሁም በስደት ለተቋቋሙ መገናኛ ብዙሃንና አክቲቪስቶች የወገነና የበለጠ ዕውቅና የሰጠ፣ ከህግና መርህ ውጪ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሲባል በተፈጸመ የተዛባ ግንኙነት ውጤት አገሪቷ ጤናማ ያልሆነ ፖለቲካዊ እንኪያ ሠላምታ፣ ብሄር ተኮር የሆነ ብሽሽቅና መዘላለፍ፣ የመጓተት፣ መጠላለፍና መጠፋፋት የሴራ ፖለቲካ ውስጥ ተዘፍቃለች፡፡

ከጅምሩ የተዛባውን ግንኙነት ተከትሎ የተፈጠረው ጤናማ ያልሆነ የሴራ ፖለቲካ በኢህአዴግ ቤትም ዘልቆ ገብቷል፡፡ የሰሞኑ ክስተት ደግሞ የአንድ ብሄረሰብ ‹ተቆሪቋሪዎች› መካከል የተጀመረው የጉልበት መፈታተሽ ቀጣይ ሆኖ ቢታይም ኢትዮጵያዊያን ለእልቂቱና ውድመቱ፣ ለፍርኃትና ሥጋት ተዳርገን ባለንበት ችግሩን በእርሱው ጓዳ ብቻ አፍኖ መያዙ ገዢው ፓርቲ/ኢህአዴግ አገሪቱ ከገባችበት የህልውና ፈተና ለመውጣት ፓርቲዎች ከመንግሥት ያላነሰ አይተኬ ሚናና ኃላፊነት አላቸው-» በሚለው የቃል ኪዳን ሰነድ የፈረመው ለፕሮፖጋንዳና ዓለምአቀፍ ግንኙነት ጥቅም እንጂ አምኖበት ያለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም መንግስት ከጅምሩ «እኔ አሻግራችኋለሁ» በሚለው አግላይ አቋሙ በመጽናት በተናጠል ያቋቋማቸው የሰላም ሚ/ርም ሆነ የዕርቅና ድንበር የመሳሰሉት ሌሎች ኮሚሽኖች መፍትሄ ሊያመጡ ቀርቶ በአግባቡ ወደ ሥራ ሊገቡ አልቻሉም ማለት ይቻላል፡፡

መንግሥት ከዚህ የመነጩ ህገወጥ ድርጊቶችን በዳተኝነት በማለፉ ዛሬ ላይ ዜጎች «መብትና ደህንነታቸውን፣የአገራቸውን ህልውና በህግ ያስከብራል» የሚለው እምነታቸው በመሸርሸሩ ተስፋቸውን እያጨለመው ነው፦ መንግሥት አለ ወይ? ብለው እንዲጠይቁም አስገድዷል፡፡ ይህ የሚያሳየው በጠቅላይ ሚ/ር ዐቢይ የሚመራው «የለውጥ ኃይል» ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል የተሰጠውን ዕድል በገባው ቃል መሰረት የህግ የበላይነትን ባከበረና ባስከበረ መንገድ ለመፈጸምና ጅምሩን ለውጥ የማስቀጠል ፈተና ላይ መውደቁን፣ የለውጡ ባቡር ሃዲዱን መሳቱ በመሆኑ፤ ጽንፍ ረገጥ፣ የጥላቻና ከፋፋይ ንግግሮች፣ ብሄርና ሃይማኖት ተኮር ግጭትና ጦር አውርድ ቅስቀሳ ከማኅበራዊ ሚዲያ አልፎ በዋና/መደበኛ ሚዲያዎች ጭምር ተስፋፍቷል፡፡

ስለዚህ ከእነዚህ የአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ መገለጫ አጣብቂኞች ለመውጣት መፍትሄው ከገዢው ፓርቲ አቅም በላይ መሆኑን ብቻ ሳይሆን መንግስት ይህን ሁኔታ በአሳታፊና ዘላቂ መንገድ ለማስተካከል ፍላጎቱም እንደሌለው ያመላክታል፤ ፓርቲያችን ይህን አደገኛ የእብሪት ጉዞ አጥብቆ ያወግዛል፣ በጽናት ይታገላል፡፡ ለዘላቂ መፍትሄው በመቻቻል ሥም መሸካከሙ፣ በሪፎርም ሥም ጥፋቱን ማድበስበሱ ችግሩን በማወሳሰብ የዜጎችን ሥቃይና ሥጋት ስለሚያራዝም "በቃ" ሊባል ይገባልና በቃ ብለናል፡፡

ፓርቲያችን ኅብር ኢትዮጵያ ጉዳዩ ከፓርቲ የሥልጣን ፉክክርም ሆነ ሥልጣን የማስቀጠል ዓላማ የአገር ኅልውናና ሉዓላዊነት፣የህዝባችን ሠላምና መብቶች መከበር እንደሚቀድም በጽኑ ያምናል፡፡ አገራችን እንደ አገር ለማስቀጠል፣ የህግ የበላይነትን በማንበር ከገባንበት የፖለቲካ

ውጥንቅጥና ውጥረት ለመውጣት ለዘላቂ መፍትሄው ሁሉም ወገን ሊወያይበት፣ ሊመክርበትና በርብርብ የየበኩሉን ሚና ሊጫወት፣ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡ በመሆኑም፡-

1) ሰሞኑን ለተፈጠረው አሰቃቂ ድረጊት ክስተትና ለደረሰው እንዲሁም፣እንደአገር ለገባንበት ፖለቲካዊ ቀውስ ተጠያቂው መንግሥት ነው፡፡ መንግስት ሁሉን የጉዳዩ ባለቤቶችን/ባድርሻዎች አካታችና አሳታፊ መድረክ በመፍጠር ለዘላቂ መፍትሄ ያለውን ቁርጠኝነት እንዲያረጋግጥ፣

2) "የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥና አጥፊዎች በህግ ፊት ቀርበው ተገቢውን፣ ሁሉ እንዲያገኙ ያለማወላወል እንሠራለን" በማለት የገባውን ቃል ከማዘናጊያነት ባለፈ በአስቸኳይ በተግባር እንዲተረጎምና ሰላምና መረጋጋት እንዲያሰፍን፤

3) የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራችን ህልውና ጉዳይ ሁላችንም ከመንግሥት የማይተናነስ ሚና እና ኃላፊነት እንዳለን በተስማማነውና በፈረምነው መሰረት በአንድ ቆመን ለዘላቂ ሠላማዊ መፍትሄ በጋራ እንድንረባረብ፣እንጠይቃለን፡፡

4) የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶች በአገርና በውጪ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን፣የሃይማኖት ተቋማት፣ ልሂቃን፣ ሲቪክ ማኅበራትና መያዶች፣ መገናኛ ብዙሃን/ሚዲያዎች፣የሙያና ህዝባዊ አደረጃጀቶች፣የአገር ሽማግሌዎች፣…ወዘተ በአጠቃላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከገባንበት አዘቅት ለመውጣት በጋራ እንድንረባረብ፣ በድጋሚ ጥሪያችን እናቀርባለን፡፡

በመጨረሻም፡- በዚህ አሰቃቂ ክስተት ለሞቱ፣ለተጎዱና ለተፈናቀሉ ወገኖችና በቤተሰቦቻቸው በደረሰው ጉዳት የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን እየገለጽን ለሟቾች ምህረትን ለቤተሰቦቻቸውና ወዳጆቻቸው መጽናናትና ብርታትን እየተመኘን፣ በተፈጠረው ክስተት፡- "ዘላቂ መፍትሄዎቻችን አገር በቀል እሴቶቻችን ላይ ይመስረቱ" እንደምንለው ከዘር፣ ኃይማኖትና ሌሎች ልዩነት አልፈው ኢትዮጵያዊያን በ"ክፉ ቀን" አንዱ የሌላው ጋሻ መከታ፣ እምባ አባሽ የመሆኑን አገራዊ እሴታችን ያስመሰከሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ያለንን አድናቆትና ክብር እንገልጻለን፤

የአገርና ህዝብ ተቆርቋሪ፣ ለሙያቸው ሥነ-ምግባር ተገዢ የሆኑ የህግ  ባለሙያዎች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው የጀመሩትን ጥረት፣ ለተጎጂዎች፣ ለሟች ቤተሰቦችና ተፈናቃዮች ሰብዐዊ ዕርዳታ ለማቅረብ ደፋ ቀና የምትሉ ኢትዮጵያዊያንን ፓርቲያችን ያደንቃል፣ ከጎናችሁ ተሰልፎ፣ በሚችለው ሁሉ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ኢሰመኮ፣ እንባ ጠባቂ፣ ኢሰመጉ፣ የኢት/ኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ዕድሮች፣ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር፣ መያዶች፣ መገናኛ-ብዙሃን፣…በጥቅሉ መላው ኢትዮጵያዊያን ከጎናቸው እንድትቆሙና እንድታግዙ ጥሪያችን እናቀርባለን፡፡

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ልጆቿን ይባርክ፣ይጠብቅ**

**ኅብር ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ [ኅብር ኢትዮጵያ]፤ ጥቅምት 18 ቀን 2012ዓ.ም፣ አዲስ አበባ**